# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 16

ሚያዝያ 28 ቀን 2014ዓም(07-05-2022)

ባለፈው ሳምንት  የአገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 15 ቅንብራችን እስከቅዳሜ ማምሻ ድረስ፤ በአገራችን የተከሰቱትን አበይት ጉዳዬች አንስተን መዘገባችንና መተቸታችን ይታወሳል።ካለፈው ሳምንት መባቻ ወዲህ ብዙ ክስተቶች የተከሰቱ ሲሆን የዛሬው ዝግጅታችን በዋና ዋናዎቹ ላይ የሚያተኩር ይሆናል።

ከሁሉም በፊት ለሁሉም ኢትዮጵያውያን እንኳን ለ81ኛው ለሚያዝያ 27 ቀን  የድል መታሰቢያ በዓል አደረሳችሁ እንላለን!

እሁድን መነሻ ብናደርገው የሙስሊም እምነት ተከታዮች ወገኖቻችን ለአንድ ወር ያህል ሲያካሂዱ የቆዩትን የሮመዳን ጾም  ለማጠናቀቅ በዋዜማው ቀን በየክፍላተ ሃገሩ በተመሳሳይ ሲያደርጉ የክርስትና እምነት ተከታዮችም በዝግጅቱ ላይ በመሳተፍ ያከናወኑትን የአደባባይ ላይ ፈጡር በአዲስ አበባ ከተማ በመስቀል አደባባይ ለማካሄድ ሲዘጋጁ ያልታሰበና ያልተጠበቀ በረዶ ያዘለ የዝናብና የንፋስ ውርጅብኝ በመከሰቱ የታሰበው ሳይሳካ ጾመኞቹ ለመበታተን ተገደዋል።በእለቱ ከደረሰው ዝናብ ለመጠለል የተጠቀሙት  የክርስቲያኑን የስጢፋኖስን  ቤተ መቅደስ ነበር።የአንዱ እምነት ለሌላው መከታና ጠለላ የመሆኑ ሂደት በዚህ ቀን ብቻ የታዬ ሳይሆን ዘመን የተሻገረ መፈቃቀድና የእኔም ነው የማለት ስሜትና ታሪክ ያለው ፤በክፉና በመከራ ቀን አንዱ ለሌላው ፈጥኖ ደራሽ የመሆንንና የአብሮነትን ባህል በገሃድ ያሳዬ ገጠመኝ ነው።

ታዲያ ይህንን አብሮነት በሚጋራው ማህበረሰብ መካከል ጸብና ቀውስ ብሎም ግጭት ከዚያም ባለፈ አገር የማፈራረስ ተልእኮ ያላቸው የውጭ ሃይሎችና የአገር ውስጥ ተባባሪዎች ከአንድ ቀን በፊት በጎንደር ከተማ በተለያዩ ቦታዎች ያደረጉት ሃይማኖት የለዬ ሁከት ያስነሳውን አለመረጋጋት ተከትሎ በሌሎቹ ያገራችን ክፍሎች በተለይም በስልጢ ወረዳ አክራሪ ሙስሊሞችን መሣሪያ ያደረገ የጸረ ኢትዮጵያ ሃይሎች የሚመሩትና ያቀነባበሩት ሁከት የኦርቶዶክስ ተዋህዶና የፕሮቴስታንትን ቤተ እምነቶች በእሳት አጋይተውና አውድመው፣ንብረትም ዘርፈው ፤ከዚያም በላይ በሰው ህይወት ላይ አደጋ አድርሰዋል።የዚሁ ጅሃዲስት አመጽና ሁከት በቀጣዩ ቀን በኢድ ዕለት ሰኞ ሚያዝያ 21 ቀን በዓሉን ተገን በማድረግ በአዲስ አበባ ከተማ በቀሰቀሱት ያልተሳካ አመጽ ብዙ ንብረት የወደመ ሲሆን አማራና ክርስቲያን ነው በሚባለውም የሁለቱም እምነቶች ተከታይ በሆነው ማህበረሰብ ላይ ያነጣጠረ ውግዘትና ጥቃት ተፈጽሟል።በዚህ አገር ጠል አመጽ የተሳተፉት ሁሉም የሙስሊም እምነት ተከታዮች አለመሆናቸው ሲታሰብ ማረጋገጫውም አመጸኞቹን በመገጸን አደብ እንዲገዙና ከሚያደርጉት እኩይ ድርጊት እንዲታቀቡ ለህይወታቸው ሳይሳሱ መሃል ገብተው ሲታገሉ የነበሩ ሃቀኛ ሙስሊሞችና አገር ወዳዶች የታዩበት ድርጊት ነበር።የእነዚህ አይነቶቹ አገር ወዳዶች ሙስሊሞች በአገር አድኑ ትግል በፋኖና ልዩሃይል እንዲሁም በመከላከያው ውስጥ ተሳትፈው ግዳጃቸውን በመፈጸም ላይ መሆናቸውን ያልተረዳው፣ቢረዳም ለባዕዳን ተልእኮ ለማስፈጸም የተሰለፈ መኖሩ ሲታይ ሆድ ካገር ይሰፋል የሚለውን አባባል ፍንትው አድርጎ ያሳያል።በቀድሞው አባባል ሆድ ካገር ይሰፋል ማለት ቻይና ታጋሽነትን ለመግለጽ ሲሆን በአሁኑ ዘመን ግን ለሆዳቸው እራሳቸውን የሸጡና አገራቸውን የከዱትን ከአገራቸው ይልቅ ሆዳቸውን የወደዱ ሆዳሞችን ማሳያ ሆኗል።

ከአንድ ቀን በፊት የዝናብና በረዶ ውርጅብኝ እንዲሁም አውሎንፋስ ያስቸገራቸው ሙስሊሞች የተጠለሉበት የስጢፋኖስ ቤተክርስቲያንም ምንም እንኳን ከፍ ያለ ጉዳት ባይደርስበትም ከአመጽ

ድንጋይ አላመለጠም።ውለታ በጥፊ ሆነና አረፈው።ያም ብቻ አይደለም ፊደል ቀርጻ ያስተማረች ቤተ ክርስቲያንና ፣የቋንቋና የአገር ባለቤት ያደረገን የአማራ ማህበረሰብ እንደ ጠላት መቁጠር ከራስ ጋር የመጣላት የመሆን እብደት እንጂ ሌላ ትርጉም አይሰጠውም።በአክራሪ ጅሃዲስቶቹ የተረሳው ነገር የአማራ ሙስሊሞች መኖራቸው ነው።በዚህ ከንቱና አገር ጠል እንቅስቃሴ የኦሮሙማው ፖለቲካ ቡድን ተሳትፎ መኖሩን የሚያሳዬው ሳያድግ ባረጀው መራራ ጉዲናና በጁዋር ሙሃመድ የሚመራው የኦሮሞ ፌዴራሊስት የሚባለው ፓርቲ ባወጣው ከቱርክ መንግሥት መግለጫ ጋር የተናበበው የተሳሳተ መግለጫ በፍኖተ ሰላም መስጊድ ተቃጠለ የሚለው በሬ ወለደ ውሸት አዘል መግለጫና በአንዋር መስጊዱ ውስጥ በተካሄደው የጀሃዲስቱ መንጋ ስብሰባ ላይ "ጁዋር ናፈቀኝ" የሚል ጫጫታ ማሰማቱ ማስረጃ ነው።ይህ ወገንተኛና ለሽብር ሃይሉ ዱላ ያቀበለ የኦፌኮ መግለጫ የፓርቲውን ከጅሃዲስቶቹ ጋር ያለውን ትስስር በግልጽ ያሳያል።በተከታታይ በተለያዩ ጊዜያቶችና ቦታዎች የተቃጠሉትን ቤተክርስቲያኖች ሳያነሳ መቅረቱ ይሉኝታ ቢስነቱን አረጋግጧል።ዱሮስ ቢሆን ከመረራና መሰሎቹ ምን ይጠበቃል?

የጅሃዲስቶቹ ፉከራና ዛቻ በመስቀል አደባባይና በመርካቶ አንዋር መስጊድ ብቻ ተወስኖ ሳይቀር በሌሎቹም ቦታዎች በተለይም ወደ ደሴ፣ሃረር፣ጅማ፣ድሬዳዋ፣ጅጅጋ---ወዘተ ተሻግሮ ለጆሮ የሚቀፉ ንግግሮችና ቅስቀሳዎች ተደምጠዋል።በአዲስ አበባው አንዋር መስጊድ ውስጥ ፋኖ ሌባ፣የሚል ሳይቀር ጸረ አማራ የፖለቲካ መልእክት የተላለፈበት መድረክ ነበር።መንግሥትና ግብረ አበሮቹ ከሚነዙት ውንጀላና ፍረጃ እንዲሁም የማጥፋት ዘመቻ የተለዬ አለመሆኑ የጅሃዲስቶቹን ከጸረ ኢትዮጵያ ከሆኑት ከኦነግ/ኦሕዴድ ብልጽግና፣ከወያኔና፣ከሌሎቹም የጎሳ ስብስብቦች ወንዝ የተቀዳ ለመሆኑ አያጠያይቅም። በተለይም በመተፎ በማይጠረጠረው ሙስሊም በሚኖርባት የደሴ ከተማ መስጊድ ውስጥ የተካሄደውና የተሰማው የጅሃዲስቶች ቅስቀሳና ፉከራ ኢትዮጵያ ውስጥ ለዚያውም ደሴ ከተማ ውስጥ ነው ለማለት አያስደፍርም። ለተመልካችና ለነዋሪው የደሴ ሕዝብ አክራሪ የእስላም መንግሥታትና ጅሃዲስቶች የሚቆጣጠሩት አገር ውስጥ እንዳለ ሆኖ ሳይሰማው አይቀርም፤እኛንም የተሰማን ስሜት በከፊል ይኸው ነው።በዚህች እስላምና ክርስቲያን ቤተሰብ ሆኖ ፣ተዋልዶና ተከባብሮ በሚኖርባት የደሴ ከተማ፣ መምጫቸው ያልታወቀ ጅሃዲስቶችና በጥቅም የተገዙ ጅሎች ቤተክርስቲያንን መስጊድ እናደርጋለን፤ እንታጠቅ፣እንዝመት፣እንግደል እያሉ በግልጽ የሚናገሩ ሰዎች ምንጫቸው ከዬት እንደሆነ ማጣራትና የማያዳግም ሕዝባዊ ቅጣት መስጠት ተገቢ ነው።ከመሪዎቹም አንዳንዶቹ መሃይሞች ሳይሆኑ ፊደል የቆጠሩ ለዛውም በሁለተኛ ደረጃና በዩኒቨርስቲ ውስጥ መምህር መሆናቸው ሲሰማ የእብደቱ ልክ ከምን እንደ ደረሰ ማሳያ ነው።እነዚህ ዲግሪ የጫኑ መሃይሞች የትምህርትን ዋጋና ደረጃ እንዲሁም ጥቅም የለሽ ያደረጉ በመሆናቸው ከተማረው ክፍል ሊቆጠሩ አይገባም።ትምህርት ህብረተሰብን ከችግርና ከመከራ የሚያወጡበት ችሎታና ዘዴ እንጂ በአውሬ መንፈስ የሰውን ልጅ ለመከራና ለአደጋ የሚነዱበት መመሪያ አይደለም።እነዚህ እብዶች የቀሩት ቁርአንም ምንና የማን እንደሆነም መመርመር አለበት፤በቅዱስ ቁርዓን ውስጥ ግን የሰፈረው የነብዩ ሙሃመድ አስተምሮ በነዚህ አካሽቲ ጅሃዲስቶች የተገለጸው ቃልና ተግባር አይደለም።እውነተኛ ሙስሊም ሃይማኖቱን ከነዚህ አይነቶቹ በካዮችና ሾይጣኖች መከላከል አለበት።ጀሃድ አስፈላጊ ሆኖም ካገኘው በነዚህ ላይ መዝመት ይኖርበታል።ነብዩም ሃይማኖትህ ከሚያረክስና ከሚያስጠላ መናጢ ጠብቅ ብለዋል።

የስልጢ ማህበረሰብም በስሙ ወንጀል የሚፈጽሙትን ለይቶ ማውጣት ይኖርበታል።በጥቂት የስልጢ ተወላጆች ምክንያት ማህበረሰቡ በሌብነትና በጅሃዲስትነት መበከል አይኖርበትም።የሰባት ቤት ጉራጌ ማፈሪያ የሆኑት ቡድኖች የወጡት ከዚህ ከስልጢው ማህበረሰብ መሆናቸው ለሁሉም የሰባት ቤት ጉራጌ ተወላጅ ማፈሪያ ሆኗል።የጉራጌ ማህበረሰብ እስላሙም ሆነ ክርስቲያኑ ለእምነቱ የቆመ፣የሰላምና የሥራ ሰው እንጂ ሌባና አጭበርባሪ ብሎም አሸባሪ ቅጥረኛና ጅሃዲስት አይደለም፣ እነ ባልቻ አባነፍሶ

የወጡበት ማህበረሰብ ለአገር አፍራሾች መከታና ዋሻ ሊሆን አይገባም።ስለሆነም የጥቂቶች መረን የለቀቀ ተግባር  የብዙሃኑን ማንነት ሲበክለው በዝምታ መታለፍ የለበትም።

በጣም የሚያሳዝነው የእስልምና ሃይማኖት ከክርስትና ሃይማኖት ከ700 ዓመት በኋላ የተፈጠረ በመሆኑ ትንሽ ዘመናዊነት ይኖረዋል ተብሎ ሲገመት ከክስርስቲያኑና ከሌሎቹም እምነቶች በፊት ወደ ነበረው የድንጋይ ዘመን የኋሊት መፈርጠጡ ሲታይ የታሪክ ጎማ ወደፊት እንጂ ወደ ኋላ አይሄድም የሚባለውን አባባል ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ አድርጎታል።በድንጋይ ዘመን ሁሉም መሣሪያ ድንጋይ ነበር፤ የአሁኖቹም ደናቁርቶች ሰውን በድንጋይ ቀጥቅጠው ሲገሉ፣ንብረት ሲያወድሙ የሚጠቀሙት በድንጋይ መሆኑ ሲታይ የድንጋይ ዘመን ሰዎች ተብለው ቢጠሩ ስህተት አይሆንም።በሳይበር ዘመን ድንጋይ የሆነ እራስ በተሸከሙ ድኩማኖች ድንጋይ ለጦር መሣሪያነት ሲውል ማዬቱ የዘመናችን  አግራሞት ሳይሆን አይቀርም። ይህ አጅሃዲስቶች እንቅስቃሴ ከጎሰኛው ስርዓት ጋር እጅና ጓንት ሆኖ ስለሚሠራ ሁለቱን ጥንድ የኢትዮጵያ ጠላቶች ለማጥፋት ቆርጦ መነሳት የግድ ይላል።አሁን ሁኔታው የበረደ ቢመስልም ጭራሽ አልጠፋም።በተለያዩ ጊዜያቶች የተለያዩ ስልት እዬመዘዘ ውዝግብና ሽብር የሚነዛው የኦሮሙማው ኦነግ መራሹ ቡድን በሙስሊሙ ትከሻ አገር የማፍረስ እቅዱን ለማስፈጸም የተጠቀመበት ያረጀና ያፈጀ ካርታ ለጊዜውም ቢሆንም የኦነግ ሸኔን እንቅስቃሴ ትኩረት እንዳያገኝ ያደረገ ስልት ሆኖ አገልግሏል።

ሰኞን ሳንሻገር ሌላው ክስተት በአብይ አህመድ ትዕዛዝ እንበለው ጥሪ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን የእምነት አባቶች በከፊል የዳግሚያ ትንሳኤውን በዓል ሰበብ አድርጎ የእራት ግብዣ በማድረግ የመደመርን ጠበል እረጭቼ አጠምቃቸዋለሁ ብሎ ያሰበው ድፍረት አለመሳካቱ አብይንና ቡድኑን ያንጨረጨረ ክስተት ነው።ራስ ፑቲን ተብሎ በሚጠራው ዳንኤል ክብረት አጋፋሪነት የታቀደው ሴራ በተጋባዦቹ ጳጳሳት ውድቅ ሲሆን ዋና ፓትሪያርኩን አቡነ ማትያስን ግን በማስገደድ ይሁን በመማለድ በቦታው እንዲገኙ ተደርጓል።ሆኖም ግን ፓትሪያርኩ ለታሰበው ሴራ ወጥመድ ሳይመቹ የራሳቸውን አቋም በማንጸባረቅ፣የመንፈስ አባትነታቸውን ተወጥተዋል።የመንግሥትንና የመሪውን አብይ አህመድን ድክመትና ተጠያቂነት ፊት ለፊት ዘርዝረዋል።ድርጊታቸው እነአብይ አህመድ ያልጠበቁት በመሆኑ ባሉበት ክው እንዲሉ አድርጓቸዋል።ብጹዕ አቡነ ማትያስም የተጠሩበትን እራት ቀርቶ ውሃ ሳይቀምሱ በመጡበት አኳኋን ተመልሰዋል።ሌሎቹ ጥቂት የሥርዓቱ ተላላኪ የሆኑ ጳጳሶችና የእምነት ተቋማት ተጠሪዎች ብቻቸውን ቀርተው አብይ አህመድ እንደ ጥንቸል ጥሻ ለጥሻ እያዞረ ስለ ጎመን እርሻው ሲሰብካቸው አምሽቶ እራታቸውን አብልቶ ወደ ዬመጡበት መልሷቸዋል።ምድረ ክርስቲያን ምእመናኑ ሲገደሉና ቤተክርስቲያናት ሲቃጠሉ ምንም ስሜት ያላደረበት አብይ አህመድ ጠራኝ ብለው የሄዱትንና በዝምታ ድጋፋቸውን የለገሱትን  የእምነት አባቶች ከግምት ውስጥ የጣለና ያጋለጠ ክስተት ነው። አብዛኞቹ ግን ከሚገፋው ምዕመናንና ከቆሙለት ተቋም ጋር በጽናት በመቆዬታቸው በምድርም በሰማይም የተከበሩ ይሆናሉ።ሞት ላይቀር መልካም ሥራ ሠርቶ መሞት ያስከብራል።ስም ከመቃብር በላይ ይውላልና ሁሉም የሃይማኖት አባቶች የአቡነ ጴጥሮስን ፈለግ ቢከተሉ ዘለዓለማዊ ክብርን ይጎናጸፋሉ።

ባለፉት ቅንብሮቻችን ደጋግመን እንዳሳዬነው የኦሮሙማው አገር የመሰልቀጥ ድፍረት በተለይም አዲስ አበባን የመዋጡ ሂደት በግልጽ እዬታዬ የመጣበት ሳምንት ነው።በአዲስ አበባ ዙሪያ በሚገኙ ትምህርትቤቶች የጀመረውን የኦነግ ባንዲራ ማንጠልጠልና የኦሮሞ መዝሙር መዘመር ግዴታ አሁን ዓይኑን በጨው አጥቦ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለመተግበር ሞክሯል።ሙከራውን ለእውነት የቆሙና የደፈሩ መምህራንና  የተማሪው ወላጆች የተቃወሙ ሲሆን ተቃውሚቸውንም ልጆቻቸውን ከትምህርት ቤቱ በማሶጣት አሳይተዋል።ይህ ድርጊት በአንድ አገርና

በአንድ የትምህርት ተቋም ውስጥ በሚማሩ የነገው አገር ተረካቢ ትውልድ ላይ የሚረጭ የጠባቦች መርዝ በጊዜው ካልተወገደ የሚያደርሰው ጉዳት ቀላል አይሆንም፤ሁሉንም ይጎዳል።የተረኞቹም ሆነ የወያኔ መሪዎች በነበረው የትምህርት ፖሊሲ ተጠቅመው በመላ አገሪቱ የመኖርና የመግባባት ብሎም ለመከበርና ለአላፊነት ቦታ መብቃታቸውን እረስተው አሁን ቁመንለታል የሚሉት ማህበረሰብ ተተኪ ትውልድ የነሱን ዕድል እንዳያገኝ ሲያደርጉ ማዬት ምን ያህል ግብዞችና እራስ ወዳዶች፣ እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል ያለችውን አህያ የተኩ መሆናቸውን በስህተት ጎዳና የሚነጉደው የማህበረሰብ ክፍል በተለይም ወጣቱ ሊያጤነው ይገባል።በዴሞክራሲ ስም ከትልቅ አገር ዜግነት አውጥተው የጠባብ ቦታ እስረኛ፣ጭፍን አገልጋይ አድርገው እንዳቆዩት፣ ከዘመኑ ጋር የተጣላ አካሄድ መሆኑን ተገንዝቦ በቃችሁ፣ በስሜ አትነግዱ ሊላቸው ይገባል።ይኸው ጉደኛ በተረኝነት የሰከረ ቡድን በአዲስ አበባ ከተማ የባለቤትነቱን ማረጋገጫ በራሱ ፍርድ ቤት፣በራሱ ቤተ መንግሥት፣በራሱ ጽ/ቤት፣በራሱ ታሪካዊ ሙዝዬም---ወዘተ ግንባታ መጠመዱ ዋና ማሳያ ነው።ግንባታም ብቻ ሳይሆን የሚያፍናቸውን ሰዎች የሚያሰቃዬውና ፍርድ የምሰጠው በራሴ የፍርድና የፍትህ ተቋም ነው ብሎ ብዙዎችም በዚህ የአረመኔዎች ተቋማት እዬታፈኑ ተሰቃይተዋል ፣እዬተሰቃዩም ነው።የሁሉም ከተማ በሆነችው አዲስ አበባ ላይ ይህንን አይነቱን እብሪት በዝምታ ማለፍ የድርጊቱ ተባባሪ መሆን ነው።ሌላውም የከተማዋ ነዋሪ በዬጎሳው በራሱ ዳኞችና ፍርድ ቤት፣በራሱ የጸጥታ ሃይሎች የመጠበቅ መብት አለኝ ብሎ ቢነሳ አግባብነት ይኖረዋል።ግን ይህ ሂደት የመለያዬቱን ጉዞ ስለሚያፋጥነውና ስለሚያጠናክረው አይመከርም።ዘመናዊ ፍትሕና ሕግ ጎሳ የለውም፣ሃይማኖትና ጾታ አይለይም።ለሁሉም ነገር የጎሳ ታፔላ መለጠፉ ሊወገዝና ሊወገድ ይገባል።የአሮሙማው የጅሎች ጉዞ የጅቦች ጋጋታ ሆኗልና መፍትሔ ይፈልጋል።ብጉር ካባበሉት ኪንታሮት ይሆናል ነውና በብጉርነቱ ማፍረጥ ከቀጣዩ ስቃይና መከራ ያድናል።

ሂደቱ በጎሰኞችና በምዕራባውያን ተባባሪዎቹ ሴራ በፈራረሰችው ዩጎዝላቪያ ውስጥ የተከሰተውን ይመስላል፤ነውም።ዩጎዝላቪያ ከተበታተነች በኋላ በጎሳ ጦርነት ፈራርሳ በከፊል በተጠገነችው በሳርዬቮ ከተማ የሚኖሩ የቦስኒያና የሰርቪያ ተወላጆች፣በእምነት ሙስሊምና ክርስቲያን የሆኑ በአንድ ቋንቋ እዬተናገሩ ተግባብተው ይኖሩ በነበሩ ዜጎች የተወለዱ ልጆች ቀደም ሲል ወላጆቻቸው በአንድነት ይሰቅሉና ይዘምሩ ከነበረው ሰንደቅ ዓላማና የሕዝብ መዝሙር ተነጥለው በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ በፈረቃ እንዲማሩ በመገደድ፣የዬጎሳቸውን ባንዲራ እዬሰቀሉና የዬራሳቸውን መዝሙር እየዘመሩ ለቀጣዩ የእርስ በርስ ጦርነት የሚረዳ የጥላቻና የጠላትነት ስሜት ይዘው እንዲያድጉ ሆኗል። የአገሪቱ መፈራረስ ለወጣቱ ጭምር የተረፈው ነገር ቢኖር ጭራሽ ድህነትና ስጋት ፣ብሎም የእርስ በርስ ግጭትና ጥላቻ ነው።እንደ ባቢሎን ግንብ ሠራተኞች የማይግባቡ የአንድ አገር ልጆች በጠላትነት የሚተያዩ ደመኞች አድርጎ ማሳደግ የሚጠቅመው ጥቂት አረመኔዎችን ብቻ ነው።ይህንን በዩጎዝላቪያ በተለይም ቦስኒያ በተባለው ክፍለሃገር ላይ የደረሰ ውድቀት እንደ ምሳሌ ወስዶ በኢትዮጵ መሬት እናስፈጽማለን ብለው የተነሱትን አረመኔዎች ለማምከን መነሳት ለነገ የማይባል ተግባርና ግዴታ ነው።በቸልታ ከታዬ ለሁሉም ነገር ይዘገይና ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ ይሆናል።ይህንን በሚመለከት የአዲስ አበባ ነዋሪ ሕዝብ በዝምታ ከተዋጠ ወደ ቁራ የሚነዳ ከብት መሆኑ አይቀርም።የዛሬው ዝምታ ለነገው የአነግና ተባባሪዎቹ ቆንጨራና ሰይፍ ሊዳርገው ይችላል። ውድቀቱም 80 ጎሳ የሚኖርባት የአዲስ አበባ ከተማ ሁለት ግፋ ቢል ሶስት ጎሳ ከሚኖርባት ከሳርዬጎ ከተማ የባሰ ይሆናል።

ከዚችው ሁሉንም ከምታስተናግድ ከአዲስ አበባ ከተማ ሳንወጣ የተረኛው ቡድን በጉልበት የተቆጣጠረው የከተማዋ አስተዳደር መሬት መቸብቸቡና ለጎሳው ተወላጆችና ለአድርባይ አጋሮቹ መከፋፈሉ ሳያንሰው አሁን ደግሞ ለለመደው ዘረፋ ያመቸኛል ብሎ ያሰበውን የከተማዋ ህንጻ በሙሉ አንድ አይነት ቀለም ይቀባ የሚል ትርክት ይዞ ብቅ ብሏል።ሕዝብ በኑሮ ውድነት ውጭ ነፍስ ግቢ ነፍስ

እያለ ሲያቃትት፣ሰላም ጠፍቶ በስጋት ሲኖር፣ ወንጀል ተስፋፍቶ ወጥቶ መግባት ባዳ በሆነበት አገርና ከተማ መረን የለቀቀ አስረሽ ምችው ድርጊት ሲከናወን አገራችን  በተለይም ከተማችን አዲስ አበባ ባለቤት አልባ እንደሆነች ማሳያ ነው።ተቃዋሚ ናቸው ወይም ለአገዛዜ አይመቹም የተባሉ ግለሰቦች እዬታፈኑ የት እንደደረሱ በማይታወቅበት አገር እዬኖሩ ሰላም አለ ማለት ዘበት ነው።እስከጊዜውም ቢሆን የሚኖረው ልቡን ያደነደነ፣ከሃዲና አድር ባይ፣ፈሪና የሥርዓቱ ደጋፊ ብቻ ነው።

በብል(ጽ)ግና ፓርቲ ውስጥ የሚታዬው ከጥቅም ጋር የተያያዘ ትርምስና የእርስበርስ ንትርክ የድርጅቱን መበስበስ የሚያሳይ ሲሆን፣ በከተማዋ አስተዳደር ውስጥ የተነሳው ውዝግብና አብይ አህመድ እራሱን ነጻ ፣ ሌሎቹን ተጠያቂ በማድረግ  የሄደበት መንገድ የድርጅቱን የመውደቅ አዝማሚያ በግልጽ ያሳያል። አብይ አህመድ እራሱ መርጦ በሾማቸው፣በራሱ ድርጅት በሆነው የብልጽግና አባላት በሆኑት የከተማዋ አስተዳዳሪዎች ላይ ጥፋቱን ሁሉ በመደፍደፍ ጣቱን ቀስሯል።በቀጣዩ ሊመታቸው ያሰባቸውን የማሶገዱ ሥራ እንደሚከተል አያጠራጥርም።

ይህን በገደል ጫፍ ላይ የተንጠለጠለ የጎሰኞች ሥርዓት ገፋ አድርጎ ገደል ለመክተት ከአሁኑ ጊዜ የተመቼ ወቅት አይኖርም።የአብይን መወገድ ብቻ ሳይሆን የጎሰኞችን ስርዓት ጠራርጎ ለማሶገድና የኢትዮጵያን ህልውና ለማስከበር  ለውጥ ፈላጊው አገር ወዳድ በአንድ ላይ ተባብሮ ግንባር መፍጠርና በቀጣዩም የሁሉም ለሁሉም በሁሉም የሆነ ጊዜያዊ መንግሥት ማቋቋም አማራጭ የሌለው ምርጫ ነው እንላለን።

ሰው ሆኖ እንደሰው የሚያስበው ዜጋ እንደ አድዋና ማይጨው አባቶቹ እምቢ ለሃገሬ እምቢ ለነጻነቴ፣ እምቢ ለኢትዮጵያዊነቱ ብሎ አሻፈረኝ ብሎ ተነስቷል።ይህንን በፋኖ ስም የተነሳሳ አገር ወዳድ ሕዝባዊ ሃይል ለማጥፋት የውጭና የውስጥ ጸረ ኢትዮጵያ ሃይሎች ተባብረው ቆመዋል።ዘመቻ ከፍተውበታል፣ ጦርነት አውጀውበታል።እነዚህ ጣምራ ጠላቶች ለመቋቋምና ድል ለማድረግ የአገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን የመፈተሻው ጊዜ አሁን ነው።

የ81 ኛው የማይጨው ጦርነትና የአምስት ዓመቱ ተጋድሎ ድል በዓል ሚያዝያ 27 ቀን እንደተቀሩት ዓመታት በታላቅ ድምቀትና አገራዊ ስሜት ተከብሮ ውሏል።የሥርዓቱ ባለቤቶች በዓሉን ለራሳቸው በሚጠቅም መልኩ ለማዘጋጀት ቢጥሩም በሕዝቡ መንፈስና ስሜት የተንጸባረቀው እልህና ወኔ የዚያ ተቃራኒ መሆኑን ታዝበናል።በተለይም በአዛውንት አርበኞችና በልጆቻቸው፤በአሁኑም ትውልድ ወጣቶች የተንጸባረቀው በወኔ የታጀበ የአገር ፍቅር ገላጭ ፉከራ ለአገራችን እንደ አገር የመቀጠሏን ተስፋ ያለመልማል።በሰልፉ ላይ የተሳተፉት የጋሞ ተወላጅ የሆኑት አዛውንት በድፍረት ለሁሉም ኢትዮጵያውያን በተለይም ለጋሞ ሕዝብ ያስተላለፉት ጥሪ፣ስለአብይ መንግሥትና ስለራሱም ያሰሙት ትችት የሁሉንም ስሜት የነካና የማንቂያ ደወል ነበር።

ያለፉትን ድሎች ስናስብ እንደ ምሳሌ አድርገን አሁንም ዳግም አድዋና  ዳግም የማይጨው ፈተና ስለተደቀነብን ሁሉም በሚችለው መንገድ ተሳትፎ ያገሩን ክብርና አንድነት የራሱንም መብትና ህልውና ማስጠበቅ አለበት የሚለው ጥሪያችንን መድገም እንሻለን።

የአባትህ ቤት ሲዘረፍ አንተም ዝረፍ በሚል ብሂል የሚመራው የብልጽግና ስብስብ በስበብ ባስባቡ በዬቦታው ዘረፋውን ተያይዞታል፤ውድድሩ ሁሉ ዘረፋና ሌብነት ሆኗል።የአዲስ አበባው አስተዳደር በግንባታና በእድሳት ስም በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ሲጨረግድ የሐረር ከተማ አስተዳደርም ከማን አንሼ በሚል ስሜት አብይ አህመድ ለማዳ ጅቦችን ለመመገብ ይመጣል በሚል ሽፋን ከተማዋን ለማደስ ብሎ መቶ ሚሊዮን ብር መመደቡን ይፋ አድርጓል።የዘመኑ ጅቦቹ እነሱ ሆነው ሳለ ለዘመናት ከሰው አፍ ላይ ቁራጭ ሥጋ ሲበሉ የሚታዩትን ጅቦች  ለመመገብ አብይ ይመጣል ብሎ ምክንያት

ማድረግ ነገሩን አያ ጅቦ ሳታመካኝ ብላኝ ወይም  በልጅ አመካኝቶ ይበላሉ አንጉቶ ያደርገዋል። ቲማቲም ገዝቶ መብላት የማይችል ሕዝብ በሚኖርባት የሐረር ከተማ ውስጥ እንዲህ አይነቱ መረን የለቀቀና የማን አለብኝ ተግባር ሲከናወን ማዬቱ ለህሊና ይከብዳል።ከነዋሪው የሰው ልጅ በላይ ጅብና ድንጋይ ክብር ሲሰጠው ከማዬት የላቀ ውርደት የለምና የሐረር ሕዝብ ዝምታና ፍርሃቱን አሸንፎ ለመብቱ መቆም አለበት እንላለን።በዝምታ ከማለቅ ሲታገሉ መሞት ዋጋ አለው፤የድልም ባለቤት ያደርጋል።

አገር ከጎሳና ከሃይማኖት በላይ ናት!

ከጎሰኝነት ነጻ የሆነ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም!!

ኢትዮጵያ በአንድነትና በነጻነት ለዘለዓለም ትኑር!!!